# የተገለጠ እውነት

የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ለመግለጥ የሚረዳ አስራ ስድስት ጠቃሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን በውስጡ የያዘ የመማሪያ መጽሐፍ

በፓውል አዳምስ እና ጆን ፊልፐስ

ትርጉም በወንድም ሰሎሞን ሐጎስ

© Paul Adams and John Phillips 2021

First edition in Amharic
Translation into Amharic coordinated by Mulugeta Ashagre

BeaconLight Trust
PO Box 91
Banstead
Surrey
SM7 9BA
United Kingdom
Email: books@beaconlight.co.uk
Website: www.beaconlight.co.uk

ISBN 978-1-906526-28-3

Design by Ben Desmond

First Edition in English © 2015 Paul Adams and John Phillips published by BeaconLight Trust

Second Edition in English ©2017 Paul Adams and John Phillips published by BeaconLight Trust

Paul Adams and John Phillips have asserted their right under the Copyright, Designs and Patents Act 1988, to be identified as authors of this work in English.

Some rights reserved. The copyright holders give free licence for this publication to be reproduced or transmitted, in any form or by any means, or stored in any retrieval system of any nature, without prior written permission provided that such use is for non-commercial purposes. Full acknowledgement of authors, publisher and source must be given.

You shall not without the copyright holders' prior written consent modify or otherwise alter this publication.

Your rights for permitted fair dealing under the Copyright, Designs and Patents Act 1988 are in no way affected by the above.

British Library Cataloguing in Publication Data

A catalogue record for this book is available from the British Library.

Acknowledgements

Material is contained in this publication for which publishing permission has been sought, and for which copyright is acknowledged. Permission to reproduce such material cannot be granted by the publishers and application must be made to the copyright holders.

Adapted from 'Truth Direct' by Paul Adams and Rick Creighton (published in 2007 by BeaconLight Trust but titled 'Life Direct' in the first edition), which was adapted from 'Directions: Fifteen Bible Study Outlines on Basic Christianity' by Norman Warren (published in 1969 by Kingsway). Used with permission.

Scriptures in this Edition are taken from the Bible in Amharic © 1962 by the United Bible Societies by kind permission of the General Secretary of the Bible Society of Ethiopia.

# የመጽሐፉ ይዘት

## መግቢያ 5

## ክፍል አንድ - ክርስቲያናዊ እምነት

1. እግዚአብሔር አብ 9
2. ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ 13
3. መንፈስ ቅዱስ 17
4. ፍጥረት 21
5. ኃጢአት 25
6. የእግዚአብሔር መፍትሄ 1 መስቀሉ 29
7. የእግዚአብሔር መፍትሄ 2፡ ትንሳኤና እርገት 33
8. ለእግዚአብሔር መፍትሄ የእኛ ምላሽ 37

## መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ፣ እግዚአብሔርን ማወቅ 41

## ክፍል ሁለት - ክርስቲያናዊ አኗኗር

9. ክርስቲያናዊ እርግጠኝነት 47
10. ክርስቲያናዊ አኗኗር የሚያስከፍለው ዋጋ 51
11. መጽሐፍ ቅዱስ 55
12. ጸሎት 59
13. ቤተ ክርስቲያን 63
14. ማምለክና ማገልገል 67
15. ሰይጣን 71
16. የኢየሱስ ዳግመኛ ምጽአት 75

# መግቢያ

## “የተገለጠ እውነት” የተዘጋጀው ለማነው?

“የተገለጠ እውነት” በዋናነት የተጻፈው ለክርስቲያኖች ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች ለሆኑ እና እንደመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መኖርን ምርጫቸው ላደረጉ ሰዎች ነው።

በተለይ ደግሞ አዳዲስ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእግዚአብሔር የተገለጡ ጠቃሚ እውነቶችን እንዲገነዘቡ ለማስቻል እጅግ በጣም ጠቃሚ ጥናት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ሳንረዳና ለሕይወታችን መሰረት አድርገን ሳንተገብራቸው ፈሪሃ እግዚአብሔር የተሞላ ሕይወት መኖር አንችልም።

ከዚህ በተጨማሪም እውነቱ ሲገለጥ ከዚህ በፊት ለተወሰኑ ጊዜያት ክርስቲያኖች የነበሩና የእምነታቸውን መሰረት እንደገና ለማደስ ወይንም ለማነቃቃት ለሚሹ ወገኖችም ጠቃሚ ጥናት ነው። ከዚህ ጥናት በሚማሩት ነገር መገረማቸው አይቀርም!

ክርስቲያን ካልሆናችሁና ምናልባትም ክርስቲያን መሆን ምን ማለት እንደሆነ ካልተረዳችሁ ጥናቶቹን በምትሰሩበት ወቅት ለብዙዎቹ ጥያቄዎቻችሁ መልስ ታገኛላችሁ። ቢሆንም ከገጽ 41 – 44 ያሉት ገጾች በተለየ መልኩ ጠቃሚ እንደሆኑ ትገነዘባላችሁ።

## የተገለጠ እውነት ጥናትን እንዴት መጠቀም ይቻላል?

ለእያንዳንዱ ጥናት የአንድ ሰዓት ጊዜ በመመደብ በግላችሁ ለማጥናት ትፈልጉ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚቻል ከሆነ የሚያስቸግሩ ነጥቦችን ሊያብራራላችሁና እርግጠኛ ያልሆናችሁበትን መልሶች ሊያረጋግጥላችሁ የሚችል የጥናት አጋዥ (ሜንቶር) ማግኘት ይኖርባችኋል፡፡

እያንዳንዱን ጥያቄ በአንድነት ሆናችሁ መመለስ ወይንም ጥያቄዎቹን በግል ከመለሳችሁ በኋላ መልሶቻችሁን ለማነጻጸር፣ አስቸጋሪ የሆኑ አሳቦችን ለመወያየትና “ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች” የሚለውን ክፍል ለመመልከት በህብረት ልትሰበሰቡ ትችላላችሁ፡፡

ሦስተኛው አማራጭ ደግሞ ጥናቶቹን በትምህርት መልኩ የሚያስጠና መሪ ማዘጋጀት ነው፡፡ ይኸውም መሪ እያንዳንዳቸው ስምንት ሳምንታትን በያዙ ሁለት ክፍሎች ጥናቱን በመክፈል በአንደኛው ክፍል ከጥናት 1-8 ያሉትን ሲሸፍን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከጥናት 9-16 ያሉትን የሚሸፍን ይሆናል፡፡

የሚቻል ከሆነ እያንዳንዱ የቡድን አባል በግሉ የአንድ ሰዓት ጊዜ በመመደብ ጥናቶቹን መስራት ሲኖርበት ሳምንታዊውም የቡድን የጥናት ጊዜ የሚከተለውን መምሰል አለበት፡

| | |
|---|---|
| የጥያቄዎቹን መልሶች መከለስ | - 35 ደቂቃ |
| “የቁልፍ እውነቶች” መወያየት | - 15 ደቂቃ |
| “ሊታሰቡባቸው የሚገቡ ጉዳዮች” በሚለው ስር ያሉትን ጥያቄዎች መመልከት | - 20 ደቂቃ |

ከላይ ከተገለጹት የጥናት መንገዶች መካከል አንዱን ወይንም ከእነዚህ ውጪ ሌላ የጥናት መንገድ ቢመረጥም ልትከተሏቸው የሚገቡ ሁለት አስፈላጊ መመሪያዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ጸሎት ነው! ጥናት ከመጀመራችሁ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በኩሉ ምን እየተናገረ እንደሆነ ለመረዳት እንድትችሉ ይረዳችሁ ዘንድ እግዚአብሔር እየጠየቃችሁ ጸልዩ። ጥናታችሁንም ከጨረሳችሁ በኋላ ከጥናቱ የተማራችሁትን በምን መልኩ ልትተገብሩት እንደሚፈልግ እንዲያሳያችሁና መተግበርም እንድትችሉ ይረዳችሁ ዘንድ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቁ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ እያንዳንዱን ጥያቄ በምትመለከቱበት ጊዜ መልሶቹን በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ከማየታችሁ በፊት የግላችሁን አመለካከት ብታስቀምጡ ጥሩ ይሆናል።

## ማስታወሻዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም (NIVUK) መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ነገር ግን የለመዳችሁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መጠቀም ትችላላችሁ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎቹ ለምሳሌ ዮሐንስ 3፡16 የሚወክሉት 3 ምዕራን ሲሆን 16 ቁጥሩን ይሆናል። ከቁጥሩ በኋላ የሚጻፈው "ሀ" ከሆነ የሚያመለክተው የጥቅሱን የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን "ለ" ከሆነ ደግሞ የጥቅሱን ሁለተኛ ክፍል ይሆናል።

# ክርስቲያናዊ እምነት

ጥናት 1-8

# እግዚአብሔር አብ

1

ሰዎች ስለእግዚአብሔር እና እርሱ ምን እንደሚመስል እንግዳ አስተሳሰብ አላቸው። እርሱ በእውነት ምን እንደሚመስል ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን መመልከት አለብን። ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ለእኛ ገልጧልና!


| እግዚአብሔር ማነው? |
| --- |
| ቆላስያስ 1:3 |

| እግዚአብሔር ለመኖሩ ምን ማስረጃ አለ? |
| --- |
| መዝሙር 19:1 |
| መዝሙር 139:13-14 |
| ዮሐንስ 20:30-31 |
| እብራውያን 1:1-3 |

# 1 • እግዚአብሔር አብ

| እግዚአብሔር ምን ይመስላል? |
|---|
| ኢሳያስ 6:3 |
| መዝሙር 90:2፣ 4 |
| መዝሙር 139:7-10 |
| ዮሐንስ 14:7-9 |
| ያእቆብ 1:17 |
| 1 ዮሐንስ 4:8 |

| እግዚአብሔር እንደሚወደን እንዴት እናውቃለን? |
| --- |
| ሮሜ 5:8 |
| 1 ዮሐንስ 4:9-10 |



## ቁልፍ እውነቶች

- እግዚአብሔር የለም ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው።
  ሰነፍ በልቡ፦ አምላክ የለም ይላል።
  መዝሙር 14:1a

- እግዚአብሔር እኛን ይወደናል። እንዲሁም ለእርሱ ፍቅር ምላሽ እንድንሰጥ ይናፍቃል።
  የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥
  1 ዮሐንስ 3:1a

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- እግዚአብሔር በእርግጥ መኖሩን በተመለከተ ለጓደኞችሁ እንዴት ነው በአሳማኝ መልኩ ልታረጋግጡለት የምትችሉት?
- "እግዚአብሔር ምን ይመስላል?" የሚል ጥያቄ ቢቀርብላችሁ በዋነኝነት የምትጠቅሷቸው የእግዚአብሔር ባሕርያት ምንድናቸው?

## ማስታወሻዎች

# ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ

# 2

ብዙዎች ከሚቀበሉት አሳብ በተቀራኒው

ኢየሱስ መኖር የጀመረው በቤትልሔም ከማሪያም በተወለደ ጊዜ አልነበረም፡፡ እርሱ ሁልጊዜ ይኖር ነበር፡፡

| ኢየሱስ ወደምድር ከመምጣቱ ስላለው ሕይወቱ ምን የምናውቀው ነገር አለ? |
| --- |
| ዮሐንስ 1:1-3 (በዚህ ክፍል “ቃል” የሚለው ቃል ኢየሱስ ማለት ነው።) |
| ቆላስያስ 1:15-17 |

| ለምንስ ነው ኢየሱስ ተብሎ የተጠራው? |
| --- |
| ማቴዎስ 1:21 |

| ኢየሱስ እውነተኛ ሰብአዊ ፍጡር መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? |
| --- |
| ሉቃስ 2:7፣ 40 |
| ሉቃስ 4:2 |

| ኢየሱስ እውነተኛ ሰብአዊ ፍጡር መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? |
|---|
| ማቴዎስ 8:23-24 |
| ዮሐንስ19:32-33 |

| ኢየሱስ እውነተኛ እግዚአብሔር መሆኑን እንዴት እናውቃለን? |
|---|
| ዮሐንስ 1:1 |
| ማርቆስ 2:5-12 |
| ማርቆስ 4:37-41 |
| ዮሐንስ11:25፣ 43-44 |

| ኢየሱስ እውነተኛ እግዚአብሔር መሆኑን እንዴት እናውቃለን? (የቀጠለ) |
| --- |
| ዮሐንስ 14:8-9 |

| ኢየሱስ ለምን ተፈተነ? ኃጢአት ሰርቷልን? |
| --- |
| እብራውያን 4:15 |

## ቁልፍ እውነቶች

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው። (የእግዚአብሔር ልጅ) እናም ከዘላለም ጀምሮ ይኖር ነበር፣ ወደፊትም ለዘላለም ይኖራል።
  በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።
  ዮሐንስ1:1

- ኢየሱስ ሰው ሆኖ በምድር ላይ ስለኖረ ፈተናዎቻችን እና የሚገጥሙንን ችግሮች በሙሉ ይረዳቸዋል።
  ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።
  እብራውያን 4:15

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ኢየሱስ ከመልካም መምህር በላይ መሆኑን በተመለከተ ለጓደኞቻችሁ በአሳማኝ መልክ እንዴት ነው የምትነግሯቸው?
- ‘ኢየሱስ ምን ይመስላል ተብላችሁ ብትጠየቁ መልሳችሁ ምን ሊሆን ይችላል?

## ማስታወሻዎች

# መንፈስ ቅዱስ

3

ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት መንፈስ ቅዱስ “ኃይል” ሳይሆን የሥላሴ ሦስተኛው አካል ነው፡ ፡ እርሱ ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዚአብሔር ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ጋር የሥላሴ ሦስተኛ አካል ነው፡፡ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኢየሱስ መንፈስ (የክርስቶስና የእግዚአብሔር ልጅ መንፈስ) ተብሎ ተጠርቷል፡፡

| መንፈስ ቅዱስ ስብእና እንዳለው የምናውቀው እንዴት ነው? |
| --- |
| ሮሜ 8:26-27 |
| ኤፌሶን 4:30 |

| መንፈስ ቅዱስን የሚገልጹ አንዳንድ ምስሎች ምንድናቸው? |
| --- |
| ዮሐንስ7:37-39፤ Acts 2:2-3 |

| እግዚአብሔር መንፈሱን የሚሰጠው ለማን ነው? |
| --- |
| ሮሜ 8:9 |


| አንዳንድ የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት ምንና ምን ናቸው? |
|---|
| ዮሐንስ 16:7-9 (ጠበቃ ወይንም በሌሎች ቅጂዎች እንደተጠቀሰው ረዳት፣ አጽናኝ፣ ወይንም አማካሪ የሚሉት ቃላት የሚናገሩት ስለመንፈስ ቅዱስ ነው።) |
| ዮሐንስ 14:25-26 |
| ሮሜ 8:26 |

| የመንፈስ ቅዱስ የመጨረሻ ግብ ምንድነው? |
|---|
| ዮሐንስ 16:14 |

| መንፈስ ቅዱስ እኛን እንደክርስቲያኖች የሚረዳን እንዴት ነው? |
|---|
| የሐዋርያት ስራ 1፡8 |
| ገላትያ 5:22-25 |

| መንፈስ ቅዱስ እኛን እንደክርስቲያኖች የሚረዳን እንዴት ነው? (የቀጠለ) |
| --- |
| 1 ቆሮንቶስ 2:10-15 |

| ከእግዚአብሔር ዘንድ ስጦታዎችን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንቀበላለን። |
| --- |
| - ስጦታዎቹ ምንድናቸው?<br>1 ቆሮንቶስ 12:8-10 |
| - ለማን ጥቅም ነው እነኝህ ስጦታዎች የሚሰጡት?<br>1 ቆሮንቶስ 12:7፣ 11 |



## ቁልፍ እውነቶች

- *መንፈስ ቅዱስ ስብእና አለው። እንዲሁም የስላሴ ሶስተኛው አካል ነው።*
  "...እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ . . . ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ . . ."
  ማቴዎስ 28:1

- *መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም አማኞች ተሰጥቷል። በዚህም የእግዚአብሔር መሆናቸው ይታወቃል።*
  . . . ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው።
  2 ቆሮንቶስ 1:21ለ-22

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- እግዚአብሔር ምን ስጦታ የሰጣችሁ ይመስላችኋል? ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም እየተገለገላችሁባቸው ነው? (ስጦታችሁን ለመለየት ትችሉ ዘንድ ክርስቲያኖችን ወይንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አነጋግሩ።)
- በእናንተ ሕይወት ውስጥ መታየት ያልጀመሩሉ "የመንፈስ ፍሬዎች" አሉን? (ገላቲያ 5፡22-23 ተመልከቱ)? (ገላትያ 5:22-23 ተመልከቱ።)

## ማስታወሻዎች

# ፍጥረት

4

የእግዚአብሔርን ሕልውና ከሚጠራጠር ሰው ጋር በሚደረግ ውይይት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የፍጥረት ጉዳይ ይነሳል። በዚህ ጥናት ፍጥረትን በተመለከተ ለሁሉም ሙግቶች መልስ መስጠት አይቻልም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለፍጥረት የሚለውን እንመለከታለን።

## በፍጥረት ውስጥ ተሳታፊ የነበረው ማነው?

ዘፍጥረት 1:1፤ ኢሳያስ 45:12

ዮሐንስ 1:1-3፤ ቆላስያስ 1:16-17

ዘፍጥረት 1:2ለ፤ መዝሙር 104:30

## የተፈጠረው ምንድነው?

ዘፍጥረት 1:1-2:3 እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ነገሮችመካከል ስድስት ነገሮችን ጥቀሱ።

## እግዚአብሔር አለምን የፈጠረው እንዴት ነው?

ዘፍጥረት 1:3 (እንዲሁም ቁጥር 6፣ 9፣ 11 እና ሌሎችም)

| እግዚአብሔር አለምን ለምን ፈጠረ? |
|---|
| መዝሙር 19:1 |

| እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ፍጥረታት በሙሉ ምን ነበር የሚያስበው? |
|---|
| ዘፍጥረት 1:31 |

| እግዚአብሔር ሰዎችን ለምን ፈጠረ? |
|---|
| ኢሳያስ 43:7 |

| እኛ ለምንድነው ልዩ የሆንነው? |
|---|
| ዘፍጥረት 1:27 |

| እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸው ኃላፊነት ምንድነው? |
| --- |
| ዘፍጥረት 1:26 |
| ዘፍጥረት 2:15 |

## ቁልፍ እውነቶች

- እግዚአብሔር አለምን ሲሰራ መልካም ነው ብሎ ተናገረ፣ ፍጹም ነበር።
  እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን።
  ዘፍጥረት 1:31

- እኛ በእግዚአብሔር አምሳል ነው የተፈጠርነው።
  እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።
  ዘፍጥረት 1:27

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራችሁን ማወቃችሁ ለእናንተ ምን ትርጉም አለው?
- የእግዚአብሔርን ፍጥረት የምንንከባከበው እንዴት ነው?

## ማስታወሻዎች

# ኃጢአት

5

ባለፈው ጥናታችን እግዚአብሔር የፈጠራት አለም ፍጹም እንደሆነች አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ ስለኃጢአት እንማራለን። ወደአለም እንዴት እንደገባ፣ በአለም ላይ ያስከተለውን ተጽእኖ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ኃጢአትን እንዴት እንደሚመለከት እናያለን።

## አሁን አለም በምን ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች?

መክብብ 1:14-15፤ ዮሐንስ 7:7

ሮሜ 8:19-22

## መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአትን እንዴት ይገልጸዋል?

ኢሳያስ 53:6

መዝሙር 106:43

## ኃጢአት ወደ ዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ የገባው መቼ ነው?

ዘፍጥረት 2:16-17፤ 3:1-7

| ኃጢአት ምንን ያካትታል? ከየት ነው የሚመጣው? |
|---|
| ማርቆስ 7:14-23 |

| እግዚአብሔር ስለኃጢአት ምን ይሰማዋል? |
|---|
| ዘፍጥረት 6:5-6 |
| ሮሜ 1:18 |

| ዛሬ በአለም ለሚታየው ኃጢአት ተወቃሹ ማነው? |
|---|
| ሮሜ 3:9-12, 23 |

| የኃጢአታችን ውጤት ምንድን ነው? |
|---|
| ሮሜ 6:23 |

| የእኛ ብቸኛው ተስፋ ምንድነው? |
| --- |
| ሮሜ 7:21-25 |

## ቁልፍ እውነቶች

- ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው። ወደአለም የመጣው በመጀመሪያዎቹ ሰዎች ነው። አዳምና ሔዋን ሆን ብለው እግዚአብሔርን አልታዘዙትም።
  ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።
  ዘፍጥረት 3፡6

- በምድር ላይ የኖረ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሰርቷል።
  ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤
  ሮሜ 3፡23

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው መልኩ ስለኃጢአት ምንነት ለጓደኛችሁ እንዴት ልታስረዱ ትችላላችሁ?
- ጓደኞቻችሁ ስለኃጢአት የሚያስቡት ምንድነው? እነርሱ ራሳቸው ኃጢአት መስራታቸውን ያስባሉ?

## ማስታወሻዎች

የእግዚአብሔር መፍትሔ

# 1 መስቀሉ

6

ባለፈው የመጨረሻ ጥናት ላይ እግዚአብሔር ስለኃጢአት ምን እንደሚያስብና ኃጢአት ምንን እንደሚያስከትል መማራችን ይታወሳል። በዚህ ጥናት ደግሞ እግዚአብሔር እኛን ከመቅጣት ይልቅ እኛን ለማዳን ስላወጣው እቅድ እንመለከታለን።

### እግዚአብሔር የእርሱ ስለሆነችው አለም ምን ያስባል?

ዮሐንስ 3፡16

### እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ወደዚህች አለም የላከው ለምንድነው?

ማርቆስ 10፡45፣ ሮሜ 5፡8፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15

### በኢየሱስ ሞት ምክንያት

- አማኞች የዳኑት ከምንድነው?

ሮሜ 5፡9

- አማኞች ያተረፉትስ ምንድነው?

ዮሐንስ 3፡16 – 17

| በኢየሱስ ስለማያምኑ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? |
| --- |
| ዮሐንስ 3፡18፣ 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-10 |

| የኢየሱስ ሞት እንዴት ነው የሚያድነን? |
| --- |
| 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24 |

| ኢየሱስ የእኛን ቅጣት በመክፈል ሂደት ውስጥ የተፈጠረበት ምንድነው? |
| --- |
| ማቴዎስ 27፡46 |
| 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21 |
| ገላትያ 3፡13 |

| ኢየሱስ በሞት ያልተሸነፈው ለምን ነበር? |
|---|
| የሐዋርያት ስራ 2፡24 |

| ጳውሎስ እንዴት ነበር ኢየሱስን የገለጸው? |
|---|
| 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5 – 6 |

## ቁልፍ እውነቶች

- ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደው ብቸኛው መንገድ ነው።
  ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።
  ዮሐንስ 14፡6

- በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኖራቸዋል። የማያምኑ ሁሉ ግን ይፈረድባቸዋል።
  በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።
  ዮሐንስ 3፡16
  በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።
  ዮሐንስ 3፡18

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ጓደኞቻችሁ ሁልጊዜ ታማኞች ስለነበሩ እና ሌሎችንም በመርዳት ይተጉ ስለነበር ልትሏቸው የሚገባችሁ ነገር ምንድነው?

- እጅግ የከፋ ወንጀል ከፈጸሙ ወንጀለኞች ውጪ እግዚአብሔር ማንንም የዘላለም ቅጣት አይቀጣም ብሎ የሚሞግት ጓደኛችሁን ምን መልስ ትሰጡታላችሁ?

## ማስታወሻዎች

የእግዚአብሔር መፍትሔ

# 2 ትንሳኤውና እርገቱ



እግዚአብሔር አብ ክርስቶስን ከሙታን አስነሳው። ስለዚህ ክርስቲያኖች የሚያምኑት ሞቶ የቀረ መምህር ሳይሆን ከሙታን የተነሳውን አዳኝና ጌታ ነው።

## የኢየሱስ ከሞት መነሳት (ትንሳኤው) ለምንድነው በጣም አስፈላጊ የሆነው?

1ኛ ቆሮንቶስ 15፡14፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡17-19

## ኢየሱስ ለመነሳቱ ምን ማስረጃ አለ?

ሉቃስ 24:1-7

ሉቃስ 24:36-43

ዮሐንስ 20:19-20

1 ቆሮንቶስ 15:5-8

| በትንሳኤው አማካኝነት የተከናወነው ምንድነው? |
| --- |
| 1 ኛ ቆሮንቶስ 15፡54 – 56 |
| ሮሜ 8፡11 |

| ትንሳኤው ስለእግዚአብሔር ምን ያስተምረናል? |
| --- |
| ኤፌሶን 1፡19 – 20 |

| ኢየሱስ ወደሰማይ ያረገው እንዴት ነበር? |
| --- |
| የሐዋርያት 1፡9 – 11 |

| አሁን ኢየሱስ የት ነው ያለው? ምን ስልጣን አለው? |
| --- |
| ኤፌሶን 1፡20 – 22 ፣ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡22 |

| አሁን ኢየሱስ ለተከታዮቹ ምን እያደረገላቸው ነው? |
| --- |
| እብራውያን 7፡25ለ |

| ከኢየሱስ ትንሳኤና እርገት የተነሳ ክርስቲያኖች ምን ተስፋ ማድረግ ይችላሉ? |
| --- |
| ዮሐንስ 14፡2 – 3 |

## ቁልፍ እውነቶች

- ትንሳኤ የእምነታችን ጠቃሚ ክፍል ነው። ኢየሱስ ከሙታን ካልተነሳ አሁንም ስለኃጢአታችን ይፈረድብናል።
  ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ ነኝ ቆሮንቶስ 15፡17፣
  አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።
  1ኛ ቆሮንቶስ 15፡20

- አሁን ኢየሱስ በሰማይ ሆኖ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እየገዛ ይገኛል። እንደካህንም ሆኖ ያገለግላል። በዚህም አገልግሎቱ እኛን ወክሎ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል፣ ይለምንልናልም።
  እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።
  እብራውያን 7፡24 – 25

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ኢየሱስ በእርግጥም ከሞት መነሳቱን በተመለከተ ጓደኛችሁን የምታሳምኑት እንዴት ነው?
- በዚህ ጥናት ውስጥ ካሉት ጥቅሶች መካከል በጣም ትልቅ መጽናናትን እና ብርታትን  የሰጧችሁ የትኞቹ ናቸው? ለምን?
- ከዚህ ጥናት የተማራችሁትና ያስገረማችሁ ነገር ይኖር ይሆንን?

## ማስታወሻዎች

# 8

# ለእግዚአብሔር መፍትሄዎች እኛ ልንሰጠው የሚገባ ምላሽ

የሕክምና ሳይንስ እና የአዳዲስ ቴክኖሎጂ እድገት የሰው ልጅ እድሜን ማራዘምና የሕይወትን ጥራት ማረጋገጥ እንደሚችል ያንጸባርቃሉ። ነገር ግን እንደሰውልጆች ለትልቁ ችግራችን ማለትም ለኃጢአት ምንም ምላሽ የለንም።

| ኃጢአት ከሚያስከትላች ችግሮች ራሳችንን ማዳን የማንችለው ለምድነው? |
| --- |
| ሮሜ 3፡20 |
| ኤፌሶን 2፡1 – 2 |

| ታዲያ ራሳችንን ማዳን የማንችል ካልሆነ እንዴት መዳን እንችላለን? |
| --- |
| ኤፌሶን 2:8-9 |

| ታዲያ ራሳችንን ማዳን የማንችል ካልሆነ እንዴት መዳን እንችላለን? |
| --- |
| ማርቆስ 1፡15ለ |

| እምነት . . .  ለምንድነው ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነው? |
| --- |
| እብራውያን 11:6 |

| እምነት . . . ኢየሱስ እንዴት ነው ሊረዳን ቃል የገባልን? |
| --- |
| ዮሐንስ 6:39 – 40 |
| ዮሐንስ 10፡ 27 – 28 |
| እብራውያን 7፡ 24 – 25 |

| ንስሐ . . . ምን ምን ያካትታል? |
| --- |
| ሕዝቅኤል 18:30 – 31 ሀ፣ የሐዋርያት ስራ 26:30 |

ንስሐ . . . ምን ምን ያካትታል?

ሉቃስ 13፡3 እና 5

ኢየሱስን ለመከተል ስንመርጥ የሕይወት መንገዳችንን የምንቀይረው እንዴት ነው?

ሮሜ 6፡15 እና 18

## ቁልፍ እውነቶች

- ድነት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነጻ ስጦታ ነው። ድነት ለማግኘት ማድረግ የሚገባን ወይንም የምንከፍለው ነገር የለም።
  ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
  ኤፌሶን 2፡8 – 9

- ያለ ንስሐ ምንም ይቅርታ የለም።
  ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።
  የሐዋርያት ስራ 2፡38

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- በመሰረቱ መልካም ሰዎች በመሆናቸው እግዚአብሔር እንደሚቀበላቸው ለሚያስቡ ጓደኞቻችሁ የምትሰጧቸው መልስ ምንድነው?
- የዳንነው በጸጋ ነው። ጸጋን እንዴት መግለጽ ትችላላችሁ?

## ማስታወሻዎች

# መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ

# መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ፣ እግዚአብሔርን ማወቅ

በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት እና በሚገባ ማወቅ በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ዓላማ መሳት ይቻላል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛ ዓላማ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን የሚገባውን ትክክለኛ ግንኙነት ማሳየት ነው።

ቀጥሎ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዴት እግዚአብሔርን በግል ማወቅ እንደሚቻል ገለጻ ቀርቧል። ይህ ገለጻ በራሳቸው እግዚአብሔርን ለማወቅ እየጣሩ ለሚገኙ ሰዎች እጅግ በጣም ይረዳቸዋል።

ክርስቲያኖች ካልሆናችሁ ማለትም የእግዚአብሔር ልጆች ካልሆናችሁ ወይንም ይህ ምን ማለት እርግጠኞች ካልሆናችሁ ወደ እውነት ሲገለጥ ሁለተኛ ክፍል ከማለፋችሁ በፊት ተከታዮቹን ማስታወሻዎች አንብቡ።

## Why are we not already in a right relationship with God?

እግዚአብሔር አለምን ሲፈጥር እኛን የሰራን በራሱ አምሳል ነበር። የዚህ ዋነኛ ምክንያትም ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንድንፈጥር እና ለእርሱ ክብር እንድትኖሩ ማድረግ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር ያቀደውን ይህን ግንኙነት አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት ውስጥ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ምክንያት የተከሰተው ኃጢአት አበላሸው። እኛም ይህን የኃጢአት ተፈጥሮ ወርሰናል።

እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስና ንጹህ ነው። ኃጢአትን በፍጹም አይታገስም። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እንዳይገናኙ የቆመ ግንብ ነበር።

> መጽሐፍ ቅዱስ
>
> **... ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤**
>
> ሮሜ 3:23

## እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚጠላ ከሆነ እርሱ እግዚአብሔር ፍቅር አይደለም ማለት ነው?

እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን በዋዛ የሚታገስ አይደለም።  ኃጢአታችን ሊቀጣ ይገባዋል።

> መጽሐፍ ቅዱስ
>
> **“የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና...”**
>
> ሮሜ 6:23 ሀ

ሆኖም እርሱ አፍቃሪና መሐሪ ነው። የእርሱ ፍቅር እጅግ ታላቅ ነው። በዚህ ምክንያትም መሻቱ እኛን ከመቅጣት ይልቅ ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት ማደስ ነው። ይህን ማሳካት የቻለውም ልጁን ኢየሱስን በመላክ ማለትም እንደሰው በምድር ላይ እንዲኖርና በእኛ ምትክ እንዲሞት በማድረግ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ

“ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።”

ሮሜ 5:8

## ያ ማለት እግዚአብሔር አይቀጣንም ማለት ነውን?

ያ ማለት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል ፈቃደኞች እስከሆንን ድረስ የእግዚአብሔርን ቅጣት አንቀበልም ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ቅጣት ዋጋ መክፈሉን ካመንን እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን መጠየቅ እንችላለን።

የኃጢአታችንን ይቅርታ መቀበልን መጽሐፍ ቅዱስ “ዳግመኛ መወለድ” ብሎ ይጠራዋል። እንደኢየሱስ ተከታይ አዲስ ሕይወት መጀመር ማለት ነው።

## ኢየሱስን ላለመቀበል ብንወስን ምን ይከሰታል?

የእግዚአብሔርን የድነት እቅድ “እምቢኝ” ብንል ቅጣት በራሳችን ላይ እንደመፈጸም ነው። ያም የሚሆነው ኢየሱስ ወደምድር ሲመለስ ነው። ምክንያቱም እርሱ የሚመለሰው እግዚአብሔር ለይቅርታ ያቀረበውን ጥሪ የማይቀበሉትን ሊፈርደባቸው ማለትም ሊቀጣቸው ነውና።

ይህም ቅጣት ከእግዚአብሔር ለዘላለም የመለየት አሰቃቂ ቅጣት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ

“... በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።”

ዮሐንስ 3:18

# ክርስቲያን ለመሆን ምን ማድረግ አለብን?

የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆንና ኃጢአታችሁ በሙሉ ይቅር እንዲባልላችሁ የሚከተሉትን መፈጸም አለባችሁ።

- የእግዚአብሔርን ሕግ አለማክበራችሁንና ለዚህም መቀጣት እንደሚገባችሁ መቀበል

- ኢየሱስ ብቻ ከእግዚአብሔር ቅጣት ሊያስመልጣችሁ እንደሚችል ማመን

- በሕይወታችሁ የፈጸማችኋቸውን ስህተቶች መናዘዝ፣ ስለእነርሱም መጸጸት ማለትም ከእነርሱ ፊታችሁን ማዞር ወይንም አቅጣጫ መቀየር

- እንደኢየሱስ ተከታዮች እግዚአብሔርን እያስደሰታችሁ ለመኖር መወሰን

እነኝህን እርምጃዎች ለመውሰድ ዝግጁዎች ከሆናችሁ የሚከተለውን ጸሎት በማድረግ ይህን መፈጸም ትችላላችሁ።

በዚህ ጸሎታችሁ እውነተኞች ከነበራችሁ እግዚአብሔር እንደልጅ ተቀብሏችኋል። የቀድሞ፣ የአሁንና የወደፊት ኃጢአታችሁ ሁሉ ይቅር ተብሎላችኋል።

ውድ እግዚአብሔር አብ፣

በሕይወቴ ከዚህ በፊት ስለሆነውና አሁንም እየሆነ ስላለው ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ሁሉ አዝናለሁ።

አሁን ስለኃጢአቴ እናዘዛለሁ።

ኢየሱስ በእኔ ፈንታ እንዲሞትና እኔ ልቀጣው ከሚገባኝ ቅጣት እንዲያስመልጠኝ ስለላከኸው አመሰግንሃለሁ።

ኢየሱስን እያስደሰትኩ ለመኖርና እርሱን የሕይወቴ ማዕከል፣ ንጉሴ ለማድረግ እፈልጋለሁ።

እባክህን ኃጢአቴን በሙሉ ይቅር ብለህ እንደልጅህ ተቀበለኝ። እባክህን አዲስ ሕይወት ይኖረኝ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ።

አሜን!

ከዚህ በኋላስ? አሁን እንደክርስቲያን ማደግ አለባችሁ። ያም ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በጥንቃቄ በሚሰጥበት ስፍራ ከክርስቲያኖች ጋር በመደበኛነት ስትገናኙ ነው። ስለዚህ የመጀመሪያው እርምጃ እናንተን በዚህ ረገድ ሊረዷችሁ ከሚችሉ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና ከክርስቲያኖች ጋር ቁርኝት መፍጠር ነው።

# ክፍል ሁለት

# ክርስቲያናዊ አኗኗር

ጥናት 9 – 16

# ክርስቲያናዊ እርግጠኝነት

9

ባለፈው ጥናታችን እምነታችንን በኢየሱስ ላይ ስናደርግና ኃጢአታችንን ተናዘን ንስሐ
ስንገባ እንደምንድን (ክርስቲያኖች እንደምንሆን) አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ በእውነት መዳናችንን እንዴት
እርግጠኞች እንደሆንን እንመለከታለን።

| መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለምን ነበር? |
| --- |
| 1ኛ ዮሐንስ 5፡13 |

| ኢየሱስ ቃል የገባልን ነገር ምንድነው? |
| --- |
| ዮሐንስ 1፡12 |
| ዮሐንስ 6፡47 |
| ዮሐንስ 10፡27 – 28 |
| ራእይ 3፡20 |

| በእውነት የእግዚአብሔር ልጆቸ ለመሆናችን እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን? |
| --- |
| ሮሜ 8፡16 |


| ኢየሱስ ሁሌም ከእኛ ጋር እንደሚሆን እንዴት እርግጠኞች እንሆናለን? |
| --- |
| ማቴዎስ 28፡20 ለ |

| እንደክርስቲያኖች መኖር መቀጠላችንን እርግጠኞች የምንሆነው እንዴት ነው? |
| --- |
| ይሁዳ 24 |

| ከክርስቶስ ፍቅር ማን ሊለየን ይችላል? |
| --- |
| ሮሜ 8፡31 - 39 |

እንደክርስቲያኖች ኃጢአት ስንፈጽም ምን ማድረግ አለብን?
እግዚአብሔርስ ይህን ስናደርግ ምን ቃል ገባልን?

1ኛ ዮሐንስ 1፥9



## ቁልፍ እውነቶች

- ኢየሱስ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሁሉ ይቀበለዋል።
  አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤
  ዮሐንስ 6፡37

- ኃጢአት ስናደርግ ድነታችንን አናጣም። ነገር ግን ኃጢኣታችንን በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ ንስሐ መግባት አለብን። ያልተናዘዝነውና ንስሐ ያልገባንበት ኃጢአት በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል ያለውን ግንኙነት እንደደመና ይጋርደዋል።
  በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።
  1ኛ ዮሐንስ 1፥9

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆናችሁ ከቶ ተጠራጥራችሁ ታውቃላችሁን? እንዲህ ከሆነ ይህን ጥርጣሬያችሁን በተመለከተ ምን አደረጋችሁ?

- ❖ እግዚአብሔር እናንተን ለኢየሱስ ክርስቶስ በመስጠቱ እግዚአብሔርን በየቀኑ ታመሰግኑታላችሁን? (ከላይ ያለውን ዮሐንስ 6፡37ን ተመልከቱ።) ይህ በየእለቱ ልናዳብረው የሚገባ ሰናይ ልማድ ነው።

## ማስታወሻዎች

# ክርስቲያናዊ አኗኗር የሚጠይቀው ዋጋ

10

ቀደም ብላችሁ እንዳያችሁት ድነት (ዘላለማዊ ሕይወት) ነጻ ስጦታ ነው። ድነት (የዘላለማዊ ሕይወት) ለማግኘት ምንም የምናደርገው ነገር የለም። ነገር ግን ይህ ጥናት ክርስቲያናዊ ሕይወትን መኖር የሚያስከፍለን እውነተኛ ዋጋ እንዳለ ያስተምረናል።

## ክርስቲያን መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

ሮሜ 12፡1 – 2

ማቴዎስ 5፡13 - 16

## ኢየሱስን ስንከተለው የምናጣው ነገር ምንድነው?

እብራውያን 12፡1

- አንዳንዶቹ በግልጽ የሚታወቁ ነገሮች ምንድናቸው?


ቆላስያስ 3፡5 – 11

| እንደክርስቶስ ደቀመዝሙሮች ልንወስዳቸው የሚገቡ አዳዲስ ነገሮች ምንደናቸው? |
|---|
| ፊልጵስዩስ 2፡1 – 5 |
| የሐዋርያት ስራ 17፡11 |
| ቆላስያስ 4፡2 |
| እብራውያን 10፡24 – 25 |
| 2 ቆሮንቶስ 8፡1 – 7፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 9፡6 – 7 |

| ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር? |
|---|
| ዮሐንስ 16፡33 ለ |

| የጥንት ክርስቲያኖች ያስተናገዱት ምን አይነት ተቃውሞ ነበር? |
| --- |
| የሐዋርያት ስራ 4:1 – 4፤ 5:17 18፤ 8፡ 1 – 3 |

| በእምነታችን ምክንያት መከራን ስንቀበል ምን ምላሽ መስጠት አለብን? |
| --- |
| 1ኛ ጴጥሮስ 4፡ 12 – 16 |



## ቁልፍ እውነቶች

- **ኢየሱስ ን መከተል ዋጋ ሊያስከፍለን ይችላል። በቀላሉ ልናየው የሚገባ ውሳኔ አይደለም**
  ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
  ሉቃስ 14:26 – 27

- **የፈተናዎችን ዋጋ ለይተን ማወቅ አለብን። እምነታችንን ከፈተኑ በኋላ ያጠናክሩታል።**
  ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት።
  ያእቆብ 1፡ 2 – 3

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- እንደክርስቶስ ተከታዮች የከፈላችሁት ከባድ ዋጋ ምንድነው?
- በአሁኑ አለም ክርስቲያኖች እንዴት ነው መከራ እየደረሰባቸውና እየተሰደዱ ያሉት? ስለእነርሱ አዘውትራችሁ ትጸልያላችሁ?
- ኢየሱስ ለኃጢአታችን የከፈለውን ዋጋ በተመለከተ ጽብረቃ አድርጉ። ፊልጵስዩስ 2፡6 – 8

## ማስታወሻዎች

# መጽሐፍ ቅዱስ

11

ክርስቲያኖች እድገታቸው ልክ እንደክርስቶስ መሆን አለበት። ለዚህም እድገት አስፈላጊ የሆነው ጠቃሚ ምግብ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ማለትም የእግዚአብሔር ቃል ነው። እግዚአብሔር የሚሻውን መልእክት በቃሉ አማካኝነት ለማስተላለፍ የተለያዩ ሰዎችን በመንፈሱ እንዲነዱ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ አደርጓቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬም ቢሆን ለኛ አስፈላጊ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ጊዜ በወሰደን ቁጥር እግዚአብሔር ሊናገረን ሁሌም ዝግጁ ነው።

| መጽሐፍ ቅዱስ ለኢየሱስ አስፈላጊው እንደነበረ የምናውቀው እንዴት ነው? |
| --- |
| ሉቃስ 4:1 – 13 |

| መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠን ለምንድነው? |
| --- |
| ዮሐንስ 20:31 |
| 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:15 – 17 |


| መጽሐፍ ቅዱስ ለኛ የተሰጠው እንዴት ነበር? |
| --- |
| 2ኛ ጴጥሮስ 1:19 – 21 |

| በሐዋርያው ጳውሎስ ጊዜ የቤርያ ክርስቲያኖች እንዴት ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ሲያጠኑ የነበሩት? |
|---|
| የሐዋርያት ስራ 17:11 |
| - ከምን አይነት ውጤት ጋር?<br>የሐዋርያት ስራ 17:12 |

| ከእግዚአብሔር ቃል ልንጠብቅ የሚገባን ምንድነው? |
|---|
| መዝሙር 119:105 |
| የሐዋርያት ስራ 20:32 |

| ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ መስጠት ያለብን እንዴት ነው? |
|---|
| ኤርምያስ 15:16 |

| ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ መስጠት ያለብን እንዴት ነው? (ካለፈው የቀጠለ) |
|---|
| መዝሙር 119፡11 |
| ያእቆብ 1፡22 – 25 |



## ቁልፍ እውነቶች

- ቃለ እግዚአብሔር የሰዎች የዘፈቀደ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ጥርቅም አይደለም። እግዚአብሔር ራሱ በመንፈሱ ቅዱሳን ሰዎችን እየነዳና እየመራ እርሱ የሚፈልገውንና እኛ እንድናውቅ የሚሻውን ነገር ብቻ በጽሑፍ እንዲያስፍሩ በማድረግ ነው የተጻፈ መጽሐፍ ነው።
  የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።
  2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16

- መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያን የእለት ተእለት ሕይወት መመሪያ መጽሐፈ እድ ነው። ችላ በማለት ልንከፍለው የምንችለው ዋጋ እጅግ በጣም ከባድ ነው።
  ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው። የጽድቅህን ፍርድ እጠብቅ ዘንድ ማልሁ፥ አጸናሁም።
  መዝሙር 119፡ 105 – 106

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- መጽሐፍ ቅዱስን በመደበኛነት ለማንበብ የምትሰጡት ቅድሚያ ምንድነው? ይህን አዳጋች እንደሆነ ካገኛችሁት ይህን በእለት ተእለት ፕሮግራማችሁ ቦታ መስጠት እንድትችሉ ምን ማድረግ ይገባችኋል?

- እግዚአብሔር እንደሚናገራችሁ እያሰባችሁ መጽሐፍ ቅዱስን ታነባላችሁ? እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት በግልጽ የተናገራችሁን ጊዜ ታስታውሳላችሁን?

## ማስታወሻዎች

# ጸሎት

12

በክርስቲያን ሕይወት ጸሎት ወሳኝ ነገር ነው። ከአባታችን ከእግዚአብሔር ጋር መደበኛ የመወያያ ጊዜ ከሌለን ጠንካራ ግንኙነት ልንመሰርት አንችልም። ይህም ከእርሱ ጋር ማውራትና እርሱን መስማትን ይጨምራል።

| ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ጸሎት አስፈላጊው እንደነበረ እንዴት እናውቃለን? |
|---|
| ማቴዎስ 14:23፣ ማርቆስ 1:35፣ ሉቃስ 6:12 |

| ጸሎት ምን ምን ያካትታል? |
|---|
| መዝሙር 32:5 |
| ፊልጵስዩስ 4:6-7 |
| ሮሜ 15:30፣ ቆላስያስ 1:9፣ ኤፌሶን 1:16-17 |

| ስለጸሎት የተሰጡ መመሪያዎች ምንድናቸው? |
| --- |
| ማቴዎስ 6:6 |
| ሉቃስ 18:1-8 |
| 1 ተሰሎንቄ 5:17 |
| እብራውያን 4:16 |

| ሐዋርያው ጳውሎስ ለሌሎች ክርስቲያኖች ከጸለያቸው ጸሎቶች ምን እንማራለን? |
| --- |
| 1 ተሰሎንቄ 5:17 ኤፌሶን 1:17፣ ቆላስያስ 1:9-10፣ ፊልጵስዩስ 1:9-11 |

| እንዴት ነው መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ የሚረዳን? |
| --- |
| ሮሜ 8:26 |

| እግዚአብሔር እንደመሻታችን ጸሎታችንን ላይለመልስልን የሚችለው እንዴት ነው? |
| --- |
| 2 ቆሮንቶስ 12:7-9 |
| ያእቆብ 4:3 |

# ቁልፍ እውነቶች

- እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለብቻችን ጊዜ እንድናሳልፍ ጥብቅ መሻቱ ነው።
  አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤
  በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።
  ማቴዎስ 6:6

- በሚያስፈልገን ጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት እንደሚሰጡን እርግጠኞች መሆን እንችላለን።
  እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው
  ዙፋን በእምነት እንቅረብ።
  እብራውያን 4:16

## ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- ከዚህ ጥናት በጸሎት ሕይወታችሁ ሊረዳችሁ የሚችል ምን ተማራችሁ?

- ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አብራችሁ መጸለይ ጀመራችሁ? ይህ በቤተ ክርስቲያን ወይንም ደግሞ ከአንድ ወይንም ከሁለት ጓደኞቻችሁ ጋር ሊሆን ይችላል። ካልሆነ ግን አሁን ልታደርጉትና ልታስቡበት የሚገባ ነገር ነው።

## ማስታወሻዎች

# ቤተ ክርስቲያን

13

"ቤተ ክርስቲያን" ሲባል ሕንጻ ማለታችን ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ እምነታችንን ያኖርን እኛ ራሳችን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነን። "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል "ጉባኤ" ወይንም "ስብስብ" ማለት ነው። ክርስቲያናዊ ቤተ ክርስቲያን በእውነተኛ አማኞች የተገነባ ነው። በአለም ሁሉ ውስጥም ተሰራጭቶ የሚገኝ ነው።

| ቤተ ክርስቲያን እንዴት ነው የተገለጸችው? |
|---|
| 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡12፣27 |
| ኤፌሶን 2፡19 – 20 |
| ኤፌሶን 5፡25 – 27 |
| 1ኛ ጴጥሮስ 2፡9 – 10 |

| የቤተ ክርስቲያን ራስ ማነው? |
|---|
| ኤፌሶን 5፡23 |

| የቤተክርስቲያን አላማ ምንድነው? |
| --- |
| የሐዋርያት ስራ 1፡8 |
| የሐዋርያት ስራ 2፡42 |
| 1ኛ ጴጥሮስ 2፡9 |

| ክርስቲያኖች በአንድነት መሰብሰብ ያለባቸው ለምንድነው? (እንደአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን) |
| --- |
| ሉቃስ 4፡16 |
| 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡21 – 27 |
| እብራውያን 10፡24 – 25 |

| እግዚአብሔር አንድነት ለመሰረትን ለእኛ ለአማኞች መሻቱ ምንድነው? |
| --- |
| ገላትያ 6፥1 – 2 |
| ኤፌሶን 4፥14 – 16 |

## ቁልፍ እውነቶች

- **ሁሉም ክርስቲያኖች ክርስቶስ ራስ የሆነለት አካል ክፍሎች ናቸው።**
  ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።
  ኤፌሶን 4፥16

- **የቤተክርስቲያን አላማ የኢየሱስ ክርስቶስን መልእክት በአለም ሁሉ ማድረስ ነው። (እኛ ያለንባቸውን ማህበረሰባት ጨምሮ።)**
  ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።
  የሐዋርያት 1፥8

## የሚታሰብባቸው ጉዳዮች

- አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አላማዋን ታሳካ ዘንድ እየረዳችኋት ነውን? (ከላይ ያለውን ተመልከቱ።) እንዴት?

- ሌሎች ክርስቲያኖችን ከፍቅርና ከበጎ ተግባር አኳያ እንዴት ነው ተጽእኖ ልትፈጥሩባቸው እየሞከራችሁና እያበረታታችኋቸው ያላችሁት? እብራውያን 10፡ 24 – 25ን ተመልከቱ።

## ማስታወሻዎች

# አምልኮና አገልግሎት

14

እግዚአብሔርን የምናመልከው ለእርሱ ያለንን ፍቅርና መስጠት እንዲሁም ለእርሱ እየታዘዝን ነው። ይህም እርሱ በእኛ ላይ ላፈሰሰው ጸጋና ፍቅር ምላሽ ነው። በሙዚቃ አማካኝነት ለእግዚአብሔር ያለንን መሰጠት መግለጥ የምንችል ቢሆንም አምልኮ ግን ከዚያ የሚበልጥ ነው። መላ ሕይወታችን ለእግዚአብሔር የምናስማርክበት ሂደት ነው። ይህም ወደመታዘዝና የፈቃደኝነት አገልግሎት ወደመስጠት ያመራል።

| እውነተኛ አምልኮ ምንድነው? |
|---|
| ሮሜ 12፡1 – 2 |

| ኢየሱስ ያገለግል የነበረው በምን አይነት አመለካከት ነበር? |
|---|
| ዮሐንስ 3፡16 |

| እኛስ በምን አመለካከት ነው አምልኳችንን መግለጽ ያለብን? |
|---|
| መዝሙር 100፡4 |
| ዮሐንስ 4፡23 – 24 |

| በሌሎች ላይ ያለን አመለካከት ምን መሆን አለበት? |
| --- |
| ዮሐንስ 13፡34 – 35 |
| ገላትያ 6፡10 |

| እንዴት ነው በስራ ላይ ያለውን እግዚአብሔር ማምለክና ማገልገል የምንችለው? |
| --- |
| ቆላስያስ 3፡22 – 25 |
| ቲቶ 2፡9 – 10 |

| በምስክርነት እግዚአብሔርን የምናገለግለው ለምንድነው? |
| --- |
| ማቴዎስ 28፡ 19 – 20 |
| 2ኛ ጴጥሮስ 3፡9 |

| እንዴት መመስከር አለብን? |
| --- |
| ማቴዎስ 5፡13 – 16 |
| ማርቆስ 5፡19 – 20 |
| 1ኛ ጴጥሮስ 3፡15 |

## ቁልፍ እውነቶች

- **ራሳችንን ሁለንተናችንን ፈቅደን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ እርሱን በእውነት እናመልከዋለን።**
  እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።
  ሮሜ 12፡1

- **ሌሎችን ከማገልገል አንጻር ትልቁን የጌታችንን የኢየሱስን ምሳሌ መከተል ይገባናል።**
  በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።
  ማርቆስ 10፡43 – 45

## የሚታሰብባቸው ጉዳዮች

- እግዚአብሔርን ከማገልገል (ከማምለክ) አኳያ በጣም ከባድ ሆኖ ያገኛችሁት ነገር ምን ነበር? (ለምሳሌ በቤታችሁ ውስጥ፣ በስራ ቦታችሁ፣ በትምህርት ቤት/በዩኒቨርሲቲ ወይንም ደግሞ ከማህበራዊ ግንኙነት አንጻር በጓደኞቻችሁ በኩል)

- እግዚአብሔርን ስታገለግሉ በኃላፊነት ስሜት ነው ወይንስ ደግሞ እግዚአብሔርን የማምለክ ተግባር እንደሆነ በማሰብ ነው?

- በሉቃስ 10፡38 – 42 ኢየሱስ በማርያና በማርታ ቤት ውስጥ የተናገረውን ነገር አንብቡ። ማርታ በእህቷ ላይ ያቀረበችውን ቅሬታ እንዴት ታዩታላችሁ? ስለኢየሱስ ምላሽስ ምን ታስባላችሁ?

## ማስታወሻዎች

# ሰይጣን

15

ሰይጣን ወይንም ዲያቢሎስ ብዙ ጊዜ የሚታሰበው የተንሻፈፈ እግር፣ ቀንድ እና ጭራ እንዳለው የካርቱን ፍጡር ተደርጎ ነው። ይህ ደግሞ እንደ ቀልድ ያለ ነገር ነው። እውነቱ ግን ሰይጣን በአንድ ወቅት ታላቅ ኃይልና ውበት የነበረው ሰማያዊ ፍጡር ነበር። ትእቢትና ስስት ውድቀትን አስከተሉበት የእግዚአብሔር እና የሰው ጠላት ሆኖም ቀረ።

| ሰይጣን እንዴት ይገለጻል? |
|---|
| ዮሐንስ 8፡44 |
| 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡14 – 15 |
| ማቴዎስ 13፡19 |
| 1ኛ ጴጥሮስ 5፡8 |

| ኢየሱስ ሰይጣንን እንዴት አሸነፈው? |
|---|
| ኤፌሶን 2፡1 – 5፤ ቆላስያስ 2፡15፤ ዕብራውያን 2፡14 -15 |

| ሰይጣን ክርስቲያኖችን የሚዋጋቸው እንዴት ነው? |
| --- |
| ማቴዎስ 4፡1 |

| ሰይጣን የማያምኑ ሰዎችን የሚዋጋቸው እንዴት ነው? |
| --- |
| 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4 |

| ክርስቲያኖች ለሰይጣን እንዴት ነው ምላሽ መስጠት ያለባቸው? |
| --- |
| ያእቆብ 4፡7 |
| 1ኛ ጴጥሮስ 5፡9 |
| ኤፌሶን 6፡11 |

| የእግዚአብሔር የጦር እቃ ምንድነው? |
| --- |
| ኤፌሶን 6፡13 – 18 |

| በመጨረሻው በሰይጣን ላይ የሚሆነው ምንድነው? |
| --- |
| ማቴዎስ 25፡41፤ ራእይ 20፡10 |

# ቁልፍ እውነቶች

- ለእኛ ለክርስቲያኖች ሰይጣን በጣም እውነት እና ንቁ ጠላታችን ስለሆነ በአንክሮ ልንወስደው ይገባናል።
  በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤
  1ኛ ጴጥሮስ 5፡8

- ሰይጣንን በጽናት መቋቋም የምንችል ከሆነ ለእግዚአብሔር ስልጣን ራሳችንን ማስገዛት አለብን።
  እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤
  ያእቆብ 4፡7

## የሚታሰብባቸው ጉዳዮች

- በሰይጣን ጥቃት ስር የነበራችሁበትን ሁኔታ ታስታውሳላችሁን? ያን ጥቃት መቋቋም ተችሏችሁ ነበርን?

- አሁንስ እንዴት ነው ራሳችሁን ከሰይጣን ለሚመጣባችሁ ጥቃት የምታዘጋጁት? ኤፌሶን 6፡13 – 18 አንብቡ

## ማስታወሻዎች

# የኢየሱስ ዳግመኛ ምጽአት

16

በትንሳኤው ምክንያት ኢየሱስ ድሮ ኃጢአትን፣ ክፋትንና ሞትን አሸነፈ። ነገር ግን በክብር ወደምድር ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ መላው የሚታየውና የማይታየው አለም ንጉስ መሆኑን  አይቀበልም። ከዚያም የታደሰ፣ የተዋጀ እና ሙሉ ፈውስ ያገኘ አዲስ ፍጥረት ይዞ ይመጣል።

| ‘በመጨረሻዎቹ ቀናት’ የኢየሱስን ዳግመኛ ምጽአት ስንጠባበቅ ልንጠነቀቅባቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድናቸው? |
| --- |
| 1ኛ ዮሐንስ 2፡18 – 26 ፤ 4፡1 – 3 |
| ገላትያ 1፡6 – 9 |
| 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡1 – 9 |

| ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ የምናውቀው እንዴት ነው? |
| --- |
| ዳንኤል 7፡13 – 14 |
| ዮሐንስ 14፡2 – 3 |

| ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ የምናውቀው እንዴት ነው? (ካለፈው የቀጠለ) |
|---|
| የሐዋርያት ስራ 1፡10 – 11 |

| ስለዳግም ምጽአቱ ምን የምናውቀው ነገር አለ? |
|---|
| ማቴዎስ 24፡44 |
| 2ኛ ጴጥሮስ 3፡10 |
| ራእይ 1፡7 |

| ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ምን ይከሰታል? |
|---|
| 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡16 – 17 |

| ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ምን ይከሰታል? (ካለፈው የቀጠለ) |
| --- |
| 1ኛ ዮሐንስ 3፡2 |

| በማይቀበሉት ላይ ምን ይደርስባቸዋል? |
| --- |
| ማቴዎስ 25፡31 – 46፤ 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡7 – 9 |

| አዲሱ ሰማይና አዲሲቱ ምድር ምን ይመስላሉ? |
| --- |
| ራእይ 21፡1 – 4 |
| ራእይ 22፡1 – 5 |

| የኢየሱስ ዳግመኛ ምጽአት የየእለት ሕይወታችን ላይ ምን ተጽእኖ ይፈጥራል? |
| --- |
| ቶቶ 2፡11 - 14 |

## ቁልፍ እውነቶች

- ብዙ ስቃይና መከራ ባለባት በዚህች አለም ክርስቲያኖች የኢየሱስን መመለስ በተስፋ መጠባበቅ አለባቸው፡፡
  እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤
  ፊልጵስዩስ 3፡20

- ለኢየሱስ ዳግመኛ ምጽአት መዘጋጀት አለብን፡፡ በማንኛውም ሰኣት ሊመጣ ይችላል፡፡
  ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፡፡
  ማቴዎስ 24፡24

## የሚታሰብባቸው ጉዳዮች

- የኢየሱስን ዳግመኛ ምጽአት በናፍቆት እየጠበቃችሁ ነው?
  ከሆነ ለምን? ካልሆነስ ለምን?

- ኢየሱስ በማንኛውም ሰአት ሊመጣ እንደሚችል ከማወቅ አንጻር በሕይወታችሁ ሊለወጥ የሚገባው ነገር አለን?

## ማስታወሻዎች

BeaconLight

biblical truth to share

Word@Work

ይህ ኢ ሜይል ከክፍያ ነጻ፣ እጅግ የተለየና ገላጭ ሲሆን የስራ ቀናችሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ኃይል ብሩህ ማድረግ የሚችል ነው።
በ198 አገራት በ30 000 ሰዎች ይነበባል።

አሁኑኑ በwordatwork.org.uk አሁኑኑ መመዝገብ ትችላላችሁ።

CrossCheck

ወንጌልን እንዴት በግልጽ ማብራራት እና ሰዎችን ሳናስጨንቅ እና ሳናስገድድ ወደ ክርስቶስ ለመምራት የሚያስችለን ቀጥተኛ እና በመስተጋብር የተሞላ ትምህርት የሚሰጥበት በይነ መረብ ነው።

ትምህርቶቹን በኦንላይን ማየት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪም ትምህርቱ በዲቪዲ እና በሕትመት መልክም በአነስተኛ ቡክሌት (መጽሐፊት) ይገኛል።

www.crosscheck.org.uk

Visit the BeaconLight website to access free resources - articles, books and Bible outlines.

BeaconLight
biblical truth to share

PO Box 91, Banstead, Surrey, SM7 9BA, United Kingdom
Email: books@beaconlight.co.uk